# ሥጋት አድሮብኛል ብያለሁ –
# አንደኛው ሥጋቴ ይህ ነው

**ደምለው አልማው**

October 8, 2016

"አንዳንድ ኢትዮጵያዊያን ከያኒያንና የታሪክ ምሁራን ስለአገራችን ለመጻፍ ሲሞክሩ መረጃዎችንና የታሪክ ዋቢዎች ፍለጋ በአውሮፓ በአረብ አገሮችመዙዋዙዋርን ማዘውተራቸው ከሚያሳዝን በላይ የራሳችንን ታሪክ ከባዕዳን መስማትና መማር ለመሸከም የሚያዳግት የኃፍረት ጫና ሆኖ ኖሮአል:: እስካሁንምአልተቃለለም::" ብለው ጽፈዋል:: በሕይወት የሚገኙ አንድ የኢትዮጵያ መሪ::

እኚህ የኢትዮጵያ መሪ የነበሩት ሰው አንድ በጽሁፋቸው ያላካተቱት ነገር ነበረ:: ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ ዋቢ ፍለጋ የተንከራተቱት ከያንያንና ታሪክጸሐፊዎች ብቻ ሳይሆኑ ዛሬ የአገሪትዋን ዕጣ-ፈንታ ያወሳሰቡት: ያባዘቱት እና መፍቻና መቁዋጠሪያ ውል ያሳጡት ፖለቲከኞች እንደዚሁ ከውጭ ባዕዳን በተገኘ ጥራዝ ዐረፍተ–ነገር የነጻነት ግንባር መስርተው ይኸው ትውልድ በተሳሳተ መንገድ ተጉዞ ጉዳዩ ከብሔረ–ሰብ አልፎ – አገረ–ሰብ- ከአገር አልፎ የምሥራቅ አፍሪቃ ከዚያም የዓለም ችግር አካል ሆኖመገኘቱን ጭምረው ቢጽፉ ኖሮ የተሙዋላ ያድረግ ነበረ እላለሁ::

ኤሪትሪያ ከእናት አገሩዋ ተበጥሳ ገነት አልገባችም:: ዛሬ እያንዳንዱ ኤሪትሪያዊ ዜጋ ከኢትዮጵያ በመለየቱ ተጠቅመዋል ወይስ ተጎድተዋል ለሚለውለእራሳቸው ለኤሪትራዊያን መተው እፈልጋለሁ:: ኤሪትራን ለዚህ ያበቃት የቅኝ ገዢዎች ሤራ ፍሬ ሲያፈራ ማየትን እንደ አብይ ምሳሌ ለመውሰድ ፈልጌነው:: በእንዲሁ ዓይነት ሞዴል በተመሳሳይ መሳ ለመሳ የተቁዋቁዋሙት የኦነግ ድርጅትም የሻዕቢያን ፈለግ ሲከተል ኖረዋል:: ወዳጃሞችም ነበሩ:: አቶሌንጮ ለታ ሕያው ምስክር ናቸው:: ከመለስ እና ከኢሳያስ ጋራ ሆነው ስንት ዓመት እንደተንከራተቱ እና በመጨረሻ እንደ እንክርዳድ አንክርድደው ሲተፉት አያሌ የኦሮሞ ወጣቶችን ለወያኔና ለሻዕቢያ ሠራዊት አስረክበው ወደመጡበት ስካንዴኔቪያ አገር የተመለሱት እኚህ የፖለቲካ ግምገማ ተደርጎባቸውአይታወቅም:: የታላቁን የኦሮሞ ኢትዮጵያዊ ጉዳይን በራሳቸውና አምስት ከማይበልጡ ጉዋዶቻቸው ጋራ እንዳሻቸው ሲያደርጉ እንደኖሩ ለመጠየቅእንኩዋን የማይፈቅዱ ተወቃሽም ተከሳሽም መሆን የማይፈልጉ ግለሰቦች ናቸው:: ታላቁን የኦሮሞ ሕዝብ ኢትዮጵያዊነትን በተሳሳተ ትርጉዋሜ ተርጉመውይኸው እስከዛሬ እየተባላንበት ለወያኔ ዕድሜ ማራዘሚያ ዓይነተኛ መሣሪያ መሆናችንን እንኩዋን በውል ሳንረዳ አለን::

እስካሁን ኦሮሞን ሴንተር አድርጎ የሚደረገው እንቅስቃሴ ስለ ሌላው ኢትዮጵያ አገርነት የሚሰማው ስሜት ማንም እንደሚያየው እና እንደሚረዳው ምንም ጥያቄ የለውም:: ኦሮሞ ኢትዮጵያዊ ነኝ እንዳይል እየተደረገ ነው:: ኢትዮጵያዊ አይደለሁኝም ለማለት ድፍረት የመጣው ከየት ነው? በማንኛውም የኦሮሞ ተቃውሞ እና ሠላማዊ ሰልፎች ላይ የጃንሆይን ባለአንበሳ: የደርግን የኢሕድሪ ዓርማ ሞፈርና ቀንበርን: የወያኔን ባለኮከብ ዓርማ ሳይሆን ኢትዮጵያ የሚተገለጥበትን የአፍሪካ ሕዝብ እንደሞዴል ወስዶ የየአገራቸው ሰንደቅ ዓላማ ያደረጉትን /ከሶማሊያና ከቦትስዋና በስተቀረ/ አህጉራዊ ክብር ያገኘውን ሦስት ቀለማትን ተጠይፎ የአንድን የፖለቲካ ድርጅት ሰንደቅ ዓላማን ብቻ መለያ አድርጎ /ምንም እንኩዋ አሁን የኦሮሞ ሕዝብ ትግል መለያ ነው ቢባልም/ መገኘት ምንድን ነው የሚባለው? ኢትዮጵያ የሚልን ፓስፖርት ተሸክሞ በተባበሩት መንግስታት እንደ አገር ያልታወቀን ስምና ባንድራ ይዞ የተባበሩት መንግስታት ደጃፍ መገኘት ምንድን ነው የሚባለው? የአገሪትዋን ብሄራዊ የሥራ ቁዋንቁዋ መናገር እንዲጠላ ማበረታታስ ከየት የመጣ የትግል ዘዴ ነው? ይህ ሁሉ አዝማሚያውስ እንዴት ነው የሚታየው? ይህን ስል ኦሮሞ በራሱ

ቁዋንቁዋ ለምን ተናገረ? ለምን ጻፈ? ለምን እንዲያድግ አደረገ? ማለቴ አይደለም:: እንዲያውም አሁን ካለበት የክልል ደረጃ አልፎ ከአማርኛ እኩል የአገሪትዋ የሥራ ቁዋንቁዋን እንዲሆን እፈልጋለሁ:: ለኦሮሞ ሕዝብ ትግልና ጥያቄ ግልጽ: ቀጥተኛ ትርጉም ያስፈልገዋል ባይ ነኝ:: አወዛጋቢ አድርጎ በውዝግብ ውስጥ እየተሽሎከሎኩ መሄድ ወይም እያደፈጡ መጉዋዝ ትክክል አይደለም:: የኦሮሞን ጥያቄ መሸፋፈንም አያስፈልግም:: ኦሮሞ ነጻነትን ይፈልጋል:: ግን ምን ዓይነት ነጻነት? ከኢትዮጵያ ሕዝብ በካርታ: በሰንደቅ ዓላማ: በሕገ- መንግስት: በወታደራዊ ኃይልና በዳር ድንበር ተለይቶ ሌላ ሉዓላዊ የሆነች አፍሪካዊ አገር መሆን ከሆነ መብቱ ነው:: የመወሰን ሥልጣኑ ግን ለእራሱ ለኦሮሞ ሕዝብ ነው መተው የሚያስፈልገው:: ነገር ግን ይህንኑ ዓላማ በኦሮሞ ሕዝብ ለማስወሰን የሚታገል ካለ ይህም መብቱ ነው:: የኦሮሞ ሕዝብ በእራሱ ስለወደፊት ዕጣ ፈንታው የሚወስንበት ነጻ አደራሽ: ነጻ አየር: ነጻ ሜዳ እንዲያገኝ መታገል ተገቢ ነው:: ያስከብራልም:: ውሽልውል የሆነ አቁዋም መያዝ አያስፈልግም:: ዛሬ የኦሮሞ ሕዝብ ማንንም የሚፈራ ሕዝብ አይደለም:: ጥቅሙና ጉዳቱን አስልቶ በድርጅት ግፊት ሳይሆን በእራሱ ስበት ተመርቶ የሚወስንበት ነጻነት እና ዴሞክራሲ ሊኖረው ይገባል:: ግን ዛሬ በድርጅት ስም ጥቂቶች ስለብዙኃኑ ለመወሰን ሩጫ ማድረግ ደግ አይደለም:: አይፈቀድምም:: ወደ ኦሮሞ ሕዝብ ሲዞሩ ሌላ ወደ ሌሎች ኢትዮጵያዊያን ሲዞሩ ሌላ ቁዋንቁዋ ወደ ዓለም ሕዝብ ሲዞሩ ሌላ ልሳን መናገር ለምን? እንደ ዶክተር መረራ ጉዲና ግልጽ አድርጎ ኦሮሞ የሚፈልገው ከሌላው ወገኑ ጋራ በእኩልነት ላይ የተመሠረተ እና እውነተኛ ፌዴራላዊ ሥርዓት ነው ብሎ በማያሻማ ሁኔታ እንደአስቀመጠው ኦነግ ለምን ግልጽ ዐረፍተ ነገር አያስቀምጥም?

ቀጥሎ እንደሚትመለከቱት ከኦነግ ዌብሳይት የተገኘ የድርጅቱ ተልእኮ ሆኖ የተቀመጠው ኦሮሞ ከአቢሲኒያ ቅኝ ግዛት ነጻ ማውጣት ይላል:: እኔ ይህንን ጽሁፍ እስከጻፍኩ ዕለት እኤአ ጥቅምት 7/2016 ዓ.ም ድረስ ከአቢሲኒያ ቅኝ ግዛት ነጻ ለመውጣት የሚል በእንግሊዘኛ እና በኦሮሚኛ ቁዋንቁዋ ሰፍሮ ይነበባል::

በነገራችን ላይ የኦሮሞ ሕዝብ ትልቁ እና ምናልባትም ታሪካዊ ስህተት አቢሲኒያ ማን እንደሆነ አለማወቁ ወይም አውቆም አለመቀበሉ ላይ ነው:: በዚህ ጉዳይ ወቅቱ ጥሩ አይደለም ብዬ እንጂ ይህንን የኦሮሞን ታሪካዊ ስህተት በተፈለገው መንገድ ለማቅረብ ዝግጁ ነኝ:: ግን ዛሬ ባይሆን ይመረጣል:: የኦሮሞ ብቻም ሳይሆን የዐምሐራ እና የትግሬ መሠረታዊ እና ግዙፍ ስህተቶች ምስጢር ሆነው መቀጠል የለባቸውም:: በዚህ ረገድ ኦሮሞ ከተሳሳተው በላይ የዐምሐራና የትግራይ ስህተቶች የሚልቁ ናቸው:: ከተፈለገ ማቅረብ ይቻላል!! እንደ እኔ እንደእኔ የምንከራከርበትና የምንከራከርለት ሕዝብ እየሞተ ስለሆነ አንገብጋቢ ጉዳይ ይቅደም እላለሁ:: ለሌላው እንደርስበታለን:: ነገር የኦሮሞ ጉዳይ የታሪካዊ ስህተቱን ጥልቀትና ስፋት እየጨመረ የመሄድ አዝማሚያ ስለሚያሰጋ ብቻ ነው የሚያናግረውም ሆነ የሚያጨቃጭቀው::

“The Oromo Liberation Front (OLF) is a political organization established in 1973 by Oromo nationalists to lead the national liberation struggle of the Oromo people against the Abyssinian colonial rule. The emergence of the OLF was a culmination of a century old yearn of the Oromo people to have a strong and unified national organization to lead the struggle.”

“Addi Bilisummaa Oromoo (ABO) jaarmayaa siyaasaa kiyyoo kolonii Habashoota jalaa bilisa bahuuf qabsoo bilisummaa ummatni Oromoo gaggeessu hogganuuf sabbontootaan bara 1973 keessa ijaaramee dha.  ABO ijaaramuun hawwi ummata Oromoo jaarraa tokkoo kan qabsoo cimaa fi waaltaawe qabaachuu dhugoomse.”

ከላይ ለመጥቀስ የሞከረኩትን ከኦነግ ድረ -ገጽ ላይ ለአስረጂ ያህል ኮፒ አድርጌ ለማሳየት ስለሞከርኩ መመልከትና ፍርዱን መስጠት ይቻላል::ይህን ከውጫሌ ውል ስምምነት የበለጠ የሚከብደውን ዐረፍተ-ነገር እንደ ተልእኮ ወስዶ ከሌሎች እትዮጵያዊያን ጋራ በእኩልነት አብሮ አገር ለመመስረት የሚለው ቃል አሻጥር ነው:: ደባ ነው:: ሤራ ነው:: ለመሆኑ ቅኝ ገዢ ማነው? ቅኝ ተገዢውስ ማነው? ከሆነስ እንዴት ቅኝ ገዢና ቅኝ ተገዢ በእኩልነት ይቆማሉ? ደግሞስ በኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት አለ? በቅኝ ያልተገዛች አገር የምንለው እያልን በአፍሪካዊያን ላይ የምንመጻደቀው የውሸት ነበረ እንዴ? በአገር ውስጥ የሚፈጠረው የአስተዳደር በደል እና ግፍ ብሎ መናገር ተገቢ ነው:: የጭቆና የአፈና ሥሮአት ነው ብሎ መናገር ትክክል ነው:: ኦነግ ቅኝ ገዛን ብሎ የጻፈው ከየት የመጣ ወራሪ ኃይል ነው? መታረም አለበት:: መስተካከልም አለበት:: በኢትዮጵያ እኩልነትን የሕግ የበላይነት እና እውነተኛ የፌደራላዊ ሥርዓት እንዲመጣ መታገል ትክክል ነው:: አይ ትክክል ነው ከተባለ ደግሞ ግልጽነት ጥሩ ነው:: ሙብትም ነው:: ምርጫም ነው:: ምንም ነገር ነውርነት የለውም:: ማንንም ማስታመም አያስፈልግም:: ድርጅቱ ካመነበት የራሱ ዓላማና ግብ ኦሮሞን ከቅኝ ግዛት ነጻ ለማውጣት ከሆነ ይታገል:: ግን አውሮፓዊያን ለኤሪትሪያና ለወሊጋ ወጣቶች ዛሬ አረጋዊያን ያቀበሉት መርዝ ቃል ኢትዮጵያን ለመበታተን ብለው ያመጡትን ሤራ ሥልጣኔ አድርጎና ተቀብሎ ትውልድን መርዞ ማፋጀት የአውሮፓዊያኑን ፍላጎት ማርካት እንጂ የኢትዮጵያዊያንን ፍላጎትና ህልም ማሳካት አይደለም::

ወደመነሻ ነጥቤ ልምጣ:: አንደኛው ሥጋቴ የኦሮሞ ሕዝብ ትግል እና የኢትዮጵያዊነት ዕጣ ፈንታ የታረቀ አይመስለኝም:: ፖለቲከኞች አላስታረቁትም:: ምሁራን ከግራም ከቀኝም ነገሩን ያከርሩታል እንጂ ሲያላሉት አይታዩም:: ለትውልዱም አውነተኛ ቅርጽና ትክክለኛ ይዘት ሰጥተው አልመሩትም:: ትውልዱም በመሰለው መንገድ በተሰማው ስሜት ትግሉን እየገፋው ይገኛል:: ይኽ ትግል ከነጉድፉ እና ከነእድፉ ጫፍ ላይ ከደረሰ እንኳ አባትክ መባባል ይመጣል::

ምክንያቱም አገር ቤት የሚገኘው የኦሮሞ ሕዝብና የፖለቲካ ድርጅቶች ይህ ችግር የሌባቸውም:: በትግሉ እሳት ውስጥ ቆመው ረመጥ ላይ እየተራመዱ የጠላት እሳት እና ጥይት እያቃጠላቸው ኦሮሞ ኢትዮጵያዊነታቸውን አጠንክረው በመታገል ላይ ናቸው:: ከማንም ኢትዮጵያዊ ጋራ ችግሮችን አስወግደው ሳይሆን ተቻችለው አብረው የመሥራት ችሎታቸውን በተግባር እያረጋገጡ ናቸው:: ችግሩ ያለው ስደተኛው ፖለቲከኞችና ስደተኛው ኦሮሞዎች ላይ ነው:: ትልቅ ሥጋት አለኝ ብዬ ከሚጠቅሳቸው ዋናውና አንዱ ውጭ ያለው ኦሮሞ ኢትዮጵያዊነት ጥያቄ ባገር ቤቱ ኦሮሞ ትውልድ እያሳደረ ያለው ጫና እና እያሳየ ያለው አረዐያነት አደጋ አለው ብዬ ስለምገምት ነው:: ሆኖም ሥጋቶችን በተለይ የኦሮሞ ኢትዮጵያዊነትን ጉዳይ በይደርስ ቢሆን እያልኩ ለማቆየት እየሞከርኩ ባለሁበት ሰዓት ወጣቱ እና ሁለገቡ ሰው ጃዋር አባቱን አላውቅም መሀመድ አያቱ እንደሆኑ ይገባኛል:: ማንንም ሳያማክር: ከማንም ጋራ ውይይትና ክርክር ሳይደረግበት ነገሮች ሳይበስሉ ባገኛቸው መድረኮች የሚናገራቸው ነገሮች ሁሉ እጅግ አሳሳቢ ናቸው::

አትላንታ ላይ ከአበበ ገላው አስቀድሞ በኦሮሚኛ ያደረገው ንግግር የኦሮሚያ ሽግግር መንግስት ቻርተር የሚያረቅቁ ምሁራኖች ሥራ እንደ ጀመሩ እንዲያውም ዶክተር አሰፋ ጃለታን እያለ ስም ጠቅሶ ሲናገር ኦሮሚያ ሠራዊት እንደሚያስፈልግው ጠቅሶ ስለነበረ አሁን ጥያቄና ውዝግብ የሚያስነሳ ሆኖ ተገኝቶአል:: ቢቢኤን ራዲዮ በሳዲቅ አህመድ ጠያቂነት ለጃዋርና ለፕሮፌሰር ሕዝቅኤል ገቢሳ ማብራሪያ እንዲሰጡበት ሲያደርግ የማዳመጥ ዕድሉን አግኝቻለሁ:: ወጣቱና ሁለገቡ ሰው ጃዋር ከአንደበቱ የወጣውን ቃል ለማስተባበል ሞከረ እንጂ አልተሳካለትም:: የተማረ ሰው ንግግር ሲሳሳት ይቅርታ ይጠይቃል:: የእኛዎቹ ይቅርታ መጠየቅ ሞትም: ነውርም: ሽንፈትም: ውርደትም ስለሚመስለን አንቀበልም:: ይህ ደግሞ የሁላችን የጋራ ባህላችን ነው:: ጃዋር ይህንኑ ባህላችንንና ባህሉን አስተጋብቶአል:: ለማስተባበል ብሎ የተጠቀማችው ቃላቶች: ዐረፍተ-ነገሮች መዘርዝሮች የሚያረኩ

አይደሉም:: የፕሮፌሰር ኅዝቅኤል መልሱም ከሁለት ማዕዘን ተነስተው በሚመጡ ሃሳቦች የሚገጥሙ ሳይሆን የሚጣረሱ ናቸው:: ስለኦሮሚያ ሽግግር መንግስት ቻርተር ረቂቅ አልሰማሁም:: ይሉና ስለኦሮሞ የወደፊት ዕጣ ፈንታ የሚወስን ኮንፈረንስ እንዳለ ይናገራሉ:: በነገራችን ላይ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚታገለውም ሆነ የማይታገለው የኦሮሞ ምሁራን የኦሮሞ ሕዝብ ቻርተር ማርቀቅ አይችልም እንደማለት ይሆን? ወይስ ዳያስፖራ ኦሮሞው ብቻውን ቀጥተኛ የትግሉ ባለቤት የሆነውን የኦሮሞ ሕዝብን ያላሳተፈና ያላማከለ ውሳኔ ለማስተላለፍ መሞከር እራሱ በመጀመሪያ ደረጃ ስህተት ነው:: የአገር ቤቱን የፖለቲካ ድርጅቶችንና ምሁራንን መናቅ ነው:: ዳያስፖራ የትግሉ አጋር እንጂ ቀጥተኛ ወሳኝ ሆኖ መገኘት ዓላማው ምን እንደሆነ ግልጽ ነው:: እንደ ወያኔዎቹ ፕሮፌሰር እንድሪያስ እሸቴ: እንደ አፈ ጉባዔ ዳዊት ዮሀንስ እና እንደ ሌሎች የህወኃት ሹመኞች በአውሮፕላን ተሳፈረው አዲስ አበባ በመግባት በልካቸው ቁመትና ስፋት የሰፉትን ሕገ- መንግስት ለመልበስ ከሆነ ዓላማው እየሞተ ያለው ኦሮሞ ማወቅ አለበት:: ለማን እንደሚሞት: ለማን በእስር እንደሚሰቃይ: ለማን ብሎ በቁም እስረኛነት እቤት እንደሚውል: ለማን ብሎ በአራት እና በአምስት ሰላዮች ተከብቦ ውሎ እንደሚያደር: ለማን ብሎ ደሙን እንደሚያፈስ: መረዳት አለበት:: የትግራይ ነጻ አውጭ ወጥቶ የኦሮሞ ነጻ አውጭ ገባ ማለት ልዩነት ምን እንደሆነ አይገባኝም:: የኦሮሞ ሕዝብ ትግል ግቡ ኦሮሚያ የምትባል አገር ለመመስረት ከሆነ ያም የሚያስከትለው አደጋ የከፋ ስለሚሆን ወያኔ እያነከሰም ቢሆን መቀጠል ያስፈልጋል የሚሉ ወገኖች አሉ ብሎ ጋዘጠኛ ጻዲቅ ሲጠይቅ: ሁለቱም የመለሱት መልስ አጥጋቢ መልስ አይደለም:: ግን ምን ይደረግ?

ኦሮሞን የሚፈሩ ኃይሎች ካሉ የራሳቸው ጉዳይ ነው:: ተወደደም ተጠላም የማይቀር ነው ብለው አስረግጠው ተናገሩ:: ስለወደፊትዋ ኢትዮጵያ ኦሮሞ ለብቻ በሕዝብ ትልቅነትና በመሬት ስፋትነት መመካትና መታበት አደጋ እንዳለው የሚጤን አይደለም? ዛሬ ደምህ ደሜ ነው ብሎ ተያይዞ ትግል ውስጥ የሚሞተው ወንድምና እህት ወገን ስሜት መጠበቅ የለበትም? አልፎ ተርፎ ይኸ ጉዳይ የሚያስጨንቀው ዐምሐራውን? ጉራጌውን? ከምባታውን? ስልጤውን? ትግሬ ወርጂውን ብቻ እንዴት ይመስላቸዋል? አሜሪካ: እንግሊዝ: እስራእል: ፈረንሳይ: ካናዳ በአጠቃላይ ኃያላኖቹ የሚያሳስባቸው አይመስላቸውም? እነዚህ ጉልበተኛ አገሮች ወያኔን ከእነእከኩ ለመሸከም የሚመርጡበት ምክንያት ለማወቅ ሙከራ ማድረግ አይገባም? አሜሪካ የኦሮሞ ሞትን ታወግዛለች:: ግን የባሰ ሞት ይዞ የሚመጣስ ካለ? ምንድን ነው ማሰተማመኛው? ዋስትናው እነጀዋር የኦሮሞን አገር ከመሰረቱ በሁዋላ የሚያዩት ጉዳይ ቢያደረጉትም: አሜሪካ ግን ከወያኔ የሚሻል ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የዜጎች እኩልነትን የሚቀበል ለማንም ማህበረሰብ እና ግለሰብ ሥጋት የማይሆን ፕሮግራምም ሆነ መፈክር በተግባር አሁኑኑ የምትፈልግ አይመስላችሁም? ለምንድን ነው ተቃዋሚዎች ወደ አንድነት ኑ እያሉ አለበለዚያ የወያኔን ፕሮፖዛል እየጠላነም ቢሆን እየቀፈፈንም ቢሆን ለመቀብል እንገደዳለን የሚሉ አይመስላችሁም? ዘላለም ጉዳዩን የጎባንና የጣውንት ብቻ አድርጎ መውሰድ ለመፎከር መዳዳት አደጋ አለው ብዬ አስባለሁ:: ሥጋቴም ይኸው ነው:: ከአርባ ዓመት በላይ የቆየን ጩኸት አሜሪካ ያልሰማችሁ ሳይሆን እየመዘነች ትርፍና ኪሣራውን እያሰላች እስካሁን ከኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች ጋራ ዘልቃለች:: እነጃዋር ፋክክር የሠፈር የሚያስመስለው ይኸረው ነው:: በሌላ ጎን እነዚህ ሁለቱ ምሁራን ይሄ ጠፍቶአቸው ነው ብዬ አልገምትም:: ካልጠፉቸውም ለምን? ይህ ዓየነቱ ግፊት ለወያኔ ዕድሜ ሰጥቶ ቆየ:: አሁንስ እንዲቀጥል ነው? አደገኛ ኮርስ የሚመስለው እዚህ ላይ ነው::

አንዳንድ ጊዜ በኦሮሞ ጉዳይ የተወሰኑ ሰዎች ብቻ እራሳቸውን ብቸኛ ወሳኝ አድርገው ባይቆጥሩ ጥሩ ይመስለኛል:: እልፍ አእላፍ ኦሮሞዎች በዕውቀትም በትምህርትም በልምድም በችሎታም እንዳሉ መገመቱ የሚበጅ ይመስለኛል:: ዕድሉ በእጄ ገባ ተብሎ በድፍረት መራመድ ጣጣው ብዙ ነው::

በኦሮሞ በኩል ስላለው ሥጋቴ ተናገርኩ እንጂ በዐምሐራ በኩል ስላለው ሌላኛው አደገኛ ሥጋት ላለማውራት ፈልጌ አይደለም::

የኦሮሞን ሕዝብ በቁዋንቁዋው መጠቀሙን የማይፈልጉ ዐማሮች አሉ:: በአገር ጉዳይ ሁለጊዜ ጠሪ እንጂ ተጠሪ መሆንን ጋባዥ እንጂ ተጋባዥ መሆንን እንደነውር የሚያዩ እልፍ ናቸው:: እንዲያውም የብሄር ጥያቄን ባን ማድረግ ነው ብሎ የተናገረው አንድ የዕድሜ ባለጸጋ ዶክተር በአንድ ዲሲ አከባቢ በተደረገው ውይይት ላይ ሲናገሩ ሰምቻቸዋለሁ::

የተከበራችሁ አንባቢዎች ሆይ: ሥጋቴ ጊዜያዊም መሠረታዊም ነው:: ተገቢም: ተገቢ ያልሆነም ሊሆን ይችላል:: የግለሰብ ነጻ አስተያየት ነው::

ጊዜያዊ ሥጋቴ የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግሉን እየመራ ነው:: ያለመሪ: ያለ ዕቅድ: ያለ ስትራቴጂ: ያለታክቲክ በንዴት ትግል ውስጥ ገብቶአል:: የሕዝብ መሪዎች ነን:: ወሳኞች ነን:: የተማርን ነን:: ዐዋቂዎች ነን:: ችግር ፈቺዎ እኛ ነን የሚሉ ሰዎች ንቅናቄውን ለመምራት ሃላፊነቱን ለመውድ ድፍረት ሲያጡ ይታያል:: እንዳይርቁትም ሊመጣ የሚችለው ድል ተቁዋዳሽ አርበኛ ለመሆን ጉጉቱም አለ:: በዚህ መካከል ሕዝብ ወደፊት እየገሰገሰ ነው:: ይሄ ነበር አሳሳቢ አስጨናቂ ጉዳይ መሆን የነበረበት:: እንዲያውም ሕዝቡን ወደ አብዮት እየመሩት ነው:: አብዮትን ማንበብና በአብዮት ውስጥ በአካል ማለፍ ልዩነቶችን አለማወቅ ወይም እራስን ነጻ ወረዳ አስቀምጦ የህዝብንና የጠላትን አቅም አመጣጠኖ የትግል ዘመቻ ለመክፈት የማያስብ የትግል መሪና አታጋይ ካለ እርሱ እራሱ የሕዝብ ጠላት ይሆናል::

ጁዋር መመከር አለበት:: ዐዋቂዎች: አባቶች: አረጋዊያን አጠገቡ ካላችሁ ምከሩት:: የኦሮሞ ሚዲያ ኔትዎርክ ኤዲቶሪያል ቦርድን አፍርሶ ተዋቂና በሳል ጋዘጠኞችን ገፍትሮ ከኦሮሞ ሕዝብ ለሚዲያ ተብሎ የሚላክለትን መረጃ ወደ ግሉ አዞሮ እራሱን ፕሮሞት እያደረገበት የሚገኘውን ሰው ነገ ኦሮሚያን ኃላፊነቱ የተወሰነ የጀዋር አገር አድርጎ የማያውጅበት ምን የሚትያስተማምን ነገር አለው? ምንም ጎበዝ:: በተለይ ኦሮሞ የሆናችሁ ዘመዶቼ በሁዋላ የሚጸጽተን ነገር እንዳይሆን?? ጭብጨባ ብዙዎችን አበላሽቶአል:: ዛሬውኑ በብስለት እንየው::

የኦሮሞ ትግል ለማንም ሥጋት እንዳይሆን ግልጽ መደረግ አለበት:: እንደ ህወኃት ወደትግራይ ሲዞሩ እና ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ እንደሚያወሩትና ዲያብሎሲያዊ አገዛዝን በሕዝባችን ላይ ጭነው እንደሚቀልዱት ዓይነት ዳግመኛ በኢትዮጵያ ምድር መከሰት የለበትም::

ስለዚህ የኦሮሞ ሕዝብ የሙብትና የነጻነት ጥያቄ ኮለል ብሎ መታየት አለበት:: በተለይ ለትግል አጋሮች::